# የዳይሬክተሮች ቦርድ የጥቆማና ምርጫ ሂደት

## (Description of the procedures to be followed for nominating directors)

**ይህ የዳይሬክተሮች ቦርድ የጥቆማ ሂደት መግለጫ በባንክ አስተዳደር መመሪያ ቁጥር SBB/91/2024 አንቀጽ 9(4) መሠረት የወጣ ነው፡፡**

### ሀ) ቅድመ ጉባኤ ተግባራት፡

1. የዳይሬክተሮች ቦርድ የጥቆማና ምርጫ መስፈርት በባንክ አስተዳደር መመሪያ ቁጥር SBB/91/2024 አንቀጽ 9(3) መሠረት **በማህበሩ ጸሐፊ** በጋዜጣ እንዲወጣ ተደርጓል፡፡
2. በባንክ አስተዳደር መመሪያ ቁጥር SBB/91/2024 አንቀጽ 9(2) መሠረት የዳይሬክተሮች ቦርድ ጊዜያዊ አስመራጭ ኮሚቴን መምረጥ ለጉባዔው ከሚቀርቡ አጀንዳዎች የመጀመሪያው እንዲሆን ይደረጋል፡፡

### ለ) በጉባዔው ዕለት የሚከወኑ ተግባራት፡

**1. ጊዜያዊ የዳይሬክተሮች ቦርድ አስመራጭ ኮሚቴን ማቋቋም**

1.1. ጊዜያዊ ኮሚቴው 5 አባላት ይኖሩታል፣

1.2. ቢያንስ 2 አባላት ተፅዕኖ ፈጣሪ ያልሆኑ ባለአክሲዮኖች ሊሆኑ ይገባል፣

1.3. የጊዜያዊ ኮሚቴው አባላት፡-

- ☞ ባለአክሲዮኖች ሊሆኑ ይገባል፣
- ☞ ጊዜያዊ የቦርድ አስመራጭ ኮሚቴ ለመሆን ፈቃደኞች ሊሆኑ ይገባል፣
- ☞ አሁን ያሉት የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት እና የባንኩ ሠራተኞች የኮሚቴው አባል መሆን አይችሉም፣
- ☞ ቢያንስ የመጀመሪያ ዲግሪ ወይም በተመጣጣኝ የትምህርት ደረጃ እውቅና ካለው ከፍተኛ የትምህርት ተቋም ያገኙ ሊሆን ይገባል፣
- ☞ በኢትዮጵያ ወይም በሌላ አገር ማህበረሰብ እንዳይጭበረበር ጥበቃ የሚሰጡ የኢትዮጵያን ወይም የሌላ አገር ሕጎችን በመጣስ በወንጀል ጥፋተኛ ያልተባሉ መሆን አለባቸው፣
- ☞ የዳይሬክተሮች ቦርድ የምርጫ ስነ-ስርዓትን የሚረዱ መሆን አለባቸው፣
- ☞ ከመካከላቸው ሰብሳቢና ፀሀፊ መምረጥ አለባቸው፡፡

## 2. ለዳይሬክተሮች ቦርድ አባልነት ጥቆማ የመስጠት ሥነ-ሥርዓት

2.1. የጊዜያዊ አስመራጭ ኮሚቴ አባላት እራሳቸውን ለዳይሬክተሮች ቦርድ ምርጫ እጩ አድርገው ማቅረብ አይችሉም፡፡

2.2. አሁን ያለው የዳይሬክተሮች ቦርድ የገለልተኛ ቦርድ እጩዎችን ዝርዝር ለጊዜያዊ አስመራጭ ኮሚቴው ማስረከብ አለበት፡፡ ይህም ቁጥር ከሚፈለገው የገለልተኛ የዳይሬክተሮች ቦርድ ሁለት እጥፍ መሆን አለበት፡፡

2.3. ጊዜያዊ አስመራጭ ኮሚቴው ለሚከተሉት 3 ዘርፎች ጥቆማ መቀበልና ዝርዝር ማዘጋጀት ይጠበቅባቸዋል፡-

ዘርፍ 1፡ 1/3ኛ የቦርድ አባላት ተፅዕኖ ፈጣሪ ካልሆኑ ባለአክሲዮኖች የሚመረጡ ሆኖ ጥቆማና ምርጫም ተፅዕኖ ፈጣሪ ባልሆኑ ባለአክሲዮኖች ብቻ ይደረጋል፡፡

ዘርፍ 2፡ 1/3ኛ የቦርድ አባላት ከሁሉም ባለአክሲዮኖች የሚመረጡ ሆኖ ጥቆማና ምርጫ በሁሉም ባለአክሲዮኖች ይደረጋል፡፡

ዘርፍ 3፡ 1/3ኛ የቦርድ አባላት ገለልተኛ ዳይሬክተሮች ቦርድ ሲሆኑ በነባሩ የዳይሬክተሮች ቦርድ ተመልምለው የሚቀርቡ ሆኖ በሁሉም ባለአክሲዮኖች ይመረጣሉ፡፡

2.4. የዕጩዎች ቁጥር ከቦርድ ብዛት ከሁለት እጥፍ ያነሰ መሆን የለበትም፡፡

2.5. የባለአክሲዮኖች መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤው ለእያንዳንዱ ዕጩ ለየብቻ ድምፅ የሚሰጥ ሲሆን ብዙ ድምፅ ያገኘ ዕጩ ይመረጣል፡፡ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ ዕጩዎች እኩል ድምፅ ቢያገኙ ምርጫው በትምህርት ደረጃ፣ በሥራ ልምድ፣ ባላቸው ችሎታ ወይም አግባብነት ባለው ማንኛውም መስፈርት ላይ ተመስርቶ ይለያል፡፡

2.6. ወደፊት ከዳይሬክተሮች ቦርድ መቀመጫ ውስጥ በተለያዩ ምክንያቶች ክፍት ወንበር በሚኖርበት ጊዜ ለመተካት እንዲያመች አሁን ያልተመረጡ ዕጩዎች በእያንዳንዱ ዘርፍ ስር ተጠባባቂ ተደርገው ይያዛሉ፡፡

2.7. የድምፅ ብዛት የሚመሰረተው ባለው የአክሲዮን/ካፒታል መጠን ላይ ነው፡፡

2.8. ሁሉም ጥቆማዎች የሚከተሉትን መረጃዎች ሊያካትቱ ይገባል፡-

- ☞ ሙሉ ስም
- ☞ ዕድሜ (ዕጩው ሕጋዊ ሰውነት ያለው ከሆነ እና ተወካዩ እዚያው የሚታወቅ ከሆነ የተወካዩን ዕድሜ)
- ☞ የትምህርት ደረጃ
- ☞ የሥራ ልምድ
- ☞ አሁን ባለው የዳይሬክተሮች ቦርድ ውስጥ ያለው የሥራ ድርሻ (ካለ)
- ☞ በማናቸውም ተቋም ውስጥ አሁን ያለው የሥራ ሁኔታ እና መደብ
- ☞ የዕጩው የመኖሪያ አድራሻ
- ☞ የጠቋሚው ባለአክሲዮን ሙሉ ስምና ያላቸው የአክሲዮን መጠን

2.9. ኮሚቴው በሁሉም ዘርፍ የተቀበለውን ጥቆማ ከተጠቋሚዎች የትምህርት ደረጃና ልምድ ጋር በአጭሩ ለባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔው መግለጽ አለበት፡፡

2.10. ኮሚቴው ዕጩዎች ለባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ ራሳቸውን እንዲያስተዋውቁ እና የቦርድ አባል ሆነው ለማገልገል ፍቃደኛ ስለመሆናቸው እንዲገልጹ ዕድል መስጠት አለበት፡፡

## 3. የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ምርጫ ሂደት

3.1. ባንኩ የምርጫ ካርድ እና የምርጫ ሳጥኖችን ያዘጋጃል፣

3.2. ባለአክሲዮኖች ለእያንዳንዱ ዘርፍ የዕጩዎችን ስም በምርጫ ካርዱ ላይ በመፃፍ በምርጫ ሳጥኖች ውስጥ ያስገባሉ፣

3.3. አንድ ባለአክሲዮን የራሱን ድርሻ ጨምሮ ከማህበሩ የተፈረመ ካፒታል ከ10% በላይ ያለን ድርሻ በመወከል መምረጥ አይችልም፣

3.4. የምርጫ ሂደቱ እንዳለቀ ኮሚቴው የምርጫ ካርዶቹን መቁጠር አለበት፣

3.5. ኮሚቴው የምርጫ ካርዶቹን ቆጥሮ ተቀባይነት የሌላቸውን ካርዶች በመለየት መመዝገብ አለበት፣

3.6. የተቆጠሩ የምርጫ ካርዶች ታሽገው ለብቻ መያዝ አለባቸው፡፡ የምርጫ ውጤቱም ለባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ ከተገለፀ በኋላ፣ የምርጫ ካርዶቹ ለማህበሩ ፀሐፊ ማስረከብ አለበት፣

3.7. የምርጫ ውጤት ወዲያው ለባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ በኮሚቴው ሰብሳቢ ወይም ፀሐፊ መገለጽ ያለበት ሲሆን የቆጠራው ሂደት ወዲያው ካላለቀ እንደሚከተለው ይስተናገዳል፡-

ሀ) ኮሚቴው እና/ወይም የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ እና የሠነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ አገልግሎት ተወካዮች፣ እንዲሁም ሌሎች አግባብነት ያላቸው በተገኙበት የምርጫ ሳጥኑ ከታሸገ በኋላ ወደ ባንኩ ዋና መሥሪያ ቤት ተወስዶ ቆጠራው በቀጣዩ የሥራ ቀን ቀጥሎ ይከናወናል፣

ለ) የምርጫውም ውጤት በባንኩ ዋና መሥሪያ ቤት የማስታወቂያ ሠሌዳ ላይ ወይም በማንኛውም የሚታይ ቦታ እና በባንኩ ድረ-ገጽ ላይ ቆጠራው በተጠናቀቀበት ዕለት ይፋ ይደረጋል፡፡

**ግሎባል ባንክ ኢትዮጵያ**

**ለጋራ ስኬታችን**